

# በኮሎምቦስ ኦሃዮ የምንገኝ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን በጠቅላይ ምኒስትር መለስ ዜናዊ የተሰማን የሐዘን መግለጫ።

የታላቅ ሰው ሞት ዘግናኝ ቢሆንም፥ ታላቅና ጀግና ሰው እንደማይነጥፍ የወንዝ ወራጅ ውሃ የማያቋርጥ ዘላለማዊ ዝክረ ታሪክ አለውና በጠቅላይ ምኒስትራችን ህልፈተ ህይወት ልባችን ቢሰበርና አምርረን ብናዝንም በመልካምና ዘላለማዊ ስራቸው እንጽናናለን ። ታድያ ግን የዘመኑ ታላቅ ሰው ብሎ ዓለም የመሰከረለት፤ ከጉያው አቅፎና ደግፎ ያሳደገው የሃገሩ ህዝብ ለኛ ሲል እንደሻማ የቀለጠ ብሎ አምርሮ ያለቀሰለት የልማት የብልጽግና፤ የሰላም፤ የፍትህና የርትዕ ኣባትና ብልህ ሃገር ወዳድ መሪ ማጣት በቃላት ለመግለጽ እማይቻል ቢሆንም እንደደንቡ የሃገራችን ህዝብ የተሰማውን ጥልቅና መሪር ሃዘን ከርቀትም ቢሆን የሕዝባችን ሃዝንና እምባ የመካፈል ታሪካዊ ወገናዊና ዜግነታዊ ግዴታ አለብንና አሁንም ርቀን ካለንበት የስደት ሃገር በታላቅ አክብሮት ለመላው ኢትዮጵያ ህዝብ፤ ለኢህአደግ መንግስሥትና እንደዚሁም ለውድ ባለቤታቸውና ልጆቻቸው ቅርብና የሩቅ ቤተዘመድና ጓደኞቻቸውን ጨምሮ ፈጣሪ ጽናቱን ይስጣቹ እያልን ለወድ አባታችን ለውድ ወንድማችንና ክቡር መሪያችንም ፈጣሪ መንግሥተሰማያት ያወርስልን ዘንድ እንጸልያለን።

የመለስ ታሪካዊ ስራዎች ለዘልአለም ህያው ሁነው ይኖራሉ!!!

\




